በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

*የተሰጠ መግለጫ*

*ታሕሣሥ 12 ቀን 2007ዓ.ም*

## *<u>በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጥቃት በዛ! እስከ መቼ?!</u>*

*ምን ጊዜም መብቱን ለማስከበር በአንድነት የማይቆምና የማይታገል የሕብረተሰብ ክፍል (ሕዝብ) ለጥቃት ይጋለጣል። ጥቃቱ በማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ገጽታዎች የሚንፀባረቅ ሊሆን ይችላል። ይህን ጥቃት ለማስወገድ የሚኬድበት የትግል ስልት እምቢተኝነት፣ አሻፈረኝ ባይነት ፣ በአንድ ቃል አመጽ ነው። አመጹ በግልም በቡድንም ሊካናወን ይችላል። ያለ አመጽ ጥቃትና በደል መቆሚያ የላቸውም። እንዲያውም ለተጠቂው መለኮታዊ መርገምና ቅጣት የወረደበት መስሎ እንዲታይ እስከሚደርስ ህሊናን ሰልቦ አሜን ብሎ መገዛትን ሊያሰርጽ የሚችልበት አጋጣሚ እንዲከሰት ሊያደርግ ይችላል።*

*ወያኔ/ኢህአዴግ በዚህ ረገድ በዘር ፖለቲካና በሌሎች ሰንካላ ምክንያቶች ሕዝቡን ከፋፍሎ ለአገዛዙ እንዲመቸው የሠራው የፖለቲካ ሸር እስካሁን እንዲቆይ ረድቶታል።በአሁኑ ጊዜ የሚታየው የሕዝብ መተባበርና በአንድነት መቆም እንዲሁም የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች ለመስዋዕትነት ቆራጥ ሆነው መታየታቸው፣ አባሎቻቸውና የሕብረተሰቡ አካላትም ተሳትፎ እየተጠናከረ መምጣቱ ብሩህ ተስፋ የሚፈነጥቅ ሆኖ ተገኝቷል።*

*ይኸ እንዳለ ሆኖ ከተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆነ ባጠቃላይ ከሕዝቡ ከዚህ በበለጠ ተጠናክሮ መገኘትና ትግሉን መልክ አሲዞ ሕዝባዊ ድልን መቀዳጀት የሚያስችል እንቅስቃሴ ይጠበቃል። ለዚህ ደግሞ ዋነኛ ጉዳይ መተባበር ነው። የፖለቲካ ድርጅቶች በበለጠ የሚቀራረቡበትና የሚተባበሩበት ከዚያም የሚዋሃዱበትን መንገድ ቢፈጥሩ የአምባገነኑ ሥርዓት ዕድሜ ማጠሪያው ሩቅ አይሆንም።*

*የሲቪል ማህበራትም በዚህ ሰላማዊ የትግል እንቅስቃሴ ግምባር ቀደም ሆነው መታየት ይኖርባቸዋል። የሲቪል ማህበራቱ በገዢው ፓርቲ ምርኮኛ ሆነው ነፃነታቸውን እንደተገፈፉ ቢታወቅም በዙሪያቸው በግዴታ የታገቱ አባላት ከዚህ የአፈና ስርዓት ለመላቀቅ በሚፈጠረው አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅመው የትግሉ ተሳታፊና ተዋናይ እንዲሆን ግድ ይላል፤ ያለበለዚያ የችግሩ ገፈት ቀማሽ ሆነው ይቀጥላሉ።*

*የኢትዮጵያ መምህራን ምንም እንኳ ማህበራቸው ኢመማ በተለጣፊ ማህበር ተብዬ እጅ ወድቆ ቢገኝም አባላቱ ባለፉት ቅርብ አመታት መብታቸውንና የሙያ ማህበራቸውን ህልውና ለማስከበር እስከ ሥራ ማቆም አድማ የደረሰ ትግል ማካሄዳቸው ይታወሳል። መምህራን በሥራ ጠባያቸው ከህብረተሰቡ ጋር ያላቸው መስተጋብር ከፍተኛ ነው። ይህን እውነታ ተጠቅመው ለሰላማዊ ትግሉ ግምባር ቀደም ሊሆኑ ይገባል። በ1966ቱ ሕዝባዊ አመጽ የነበራቸውን አኩሪ የትግልና የመስዋዕትነት ድርሻ በአሁኑ ጊዜም እንዲደግሙት የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጊዜን በማመንታት እንዳናጠፋ ያስገድዳል።*

*በዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች ተካተው የሚገኙትን የሰብአዊ መብቶች ማለትም በነፃ የመደራጀት ፣ የመሰብሰብ፣ ሐሰብን በነፃ የመግለጽ ፣ ሥራ የማቆም አድማ ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና -------የመሳሰሉት በምንም መልኩ በመንግሥት ስም በተቀመጠ አምባገነን ጨፊጫፊ ቡድን ሊገሰሱ አይገባም፤ ይህ እንዲቀጥል መፈቀድም የለበትም።በኢትዮጵያ የሚታየው ከዚያም በላይ ሆኖ አገሪቱ እንደ አገር ሕዝቡም እንደ ሕዝብ የመቀጠል ሁኔታ የህልውና ጥያቄ ከሆነ ቆይቷል።*



P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

*በሁሉም መስክ የተማረረው  የህብረተሰብ  ክፍል ምሬቱንና ብሶቱን አደባባይ አውጥቶ ብሔራዊ አጀንዳ አድርጎታል። አምባገነኑ ሥርዓት  ደግሞ ይህን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለማፈን የኃይል እርምጃ ለመውሰድ የተፈጥሮ ባህርዩና የውንብድና ልምዱ ስለሆነ ቀጥሎበታል።የዓለም አቀፉን ማህብረተሰብ በቅጥፈት ፕሮፖጋንዳ ማደናገሩንም እንዲሁ።*

*በዚሁ ላይ ለራሳቸው ጂኦፖለቲካ ሲሉ ሁለገብ ርዳታ የሚለግሱት ባዕድ መንግሥታትም ይህ አሻንጉሊት ሥርዓት እንዲቆይ የሚሸርቡት ሴራ የሕዝባችንን ስቃይ በማራዘም ሂደት ድርሻ አለው። ሆኖም ግን ዘለቄታ የማይኖረውና በሕዝብ አሸናፊነት የሚወገድ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ታንክ፣ መድፍና መትረየስ በህዝባዊ አመጽ ይዋጣሉና።*

*ሕዳር 27 ቀን 2007 ዓ.ም  9ኙ ተቃዋሚ ድርጅቶች ትብብር የጠረው የአደባባይ የአዳር የተቃውሞ ስብሰባ ወቅት ወያኔ በፈጸመው ድብደባ፣ወከባ፣እንዲሁም አስራት የሕዝብን መብትና ሉዓላዊነት ደፍሯል። አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችንም በገሃድ ጥሷል። በሕዝብ ላይ በተጫነው የይስሙላ ሕገ መንግሥት የተከተቱ የራሱን ሕጎች ሳይቀር ደፍጥጦ ሕገ መንግሥቱን ለመናድ እያለ ያላግጣል፣ያጭበረብራል ፣ተቃዋሚውንም ሁሉ ይወነጅላል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ታህሣሥ 10 ቀን 2007 ዓ.ም በባሕዳር ከተማ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የጥምቀት በዓል የሚያከሩበት ቦታ ለልማት በሚል ሸፋን በመወሰዱ ሕዝቡ ተቃውሞውን በሰላማዊ መንገድ ለመግለጽ በመውጣቱ በወያኔ የአጋዚ ጦር ሕፃናት፣ አረጋውያን፣--- በግፍ ተገድለዋል።በርከታ ቆስለዋል። ወጣቶች ከየቤታቸው እየታፈሱ ናቸው። ይህን ዓይን ያወጣ የፋሺስት ግድያ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ በጥብቅ ያወግዛል። ለነገሩ ወያኔ/ኢህአዴግ በተለያዩ ጊዜያት ግድያን ጨምሮ ብዙ ዓይነት ግፎችን በዜጎች ላይ ሲፈጽም የቆየ ስለሆነ እንደ ዱብ ዕዳ ባይቆጠርም ጥቃቱ ሁሉንም ዜጎች በቦታ፣ በፆታ፣ በኃይማኖት፣ በሙያ መስክ ------ ሳይለይ ያከተተ ስለሆነ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጥቃት በዛ!እስከ መቼ?ı የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ለዚህ መልሱ ሁሉም በግል እየተካሄደ ያለውን ትግል አገራዊ መልክ በማስያዝ በጋራ ወያኔ ላይ መነሳት ፣ ትግሉን በቀጣይነት ማካሄድ ፣አገርና ህዝብን ከሁሉም በላይ ማስቀደም ነው። የፖለቲካና ሲቪክ ድርጅቶች እንዲሁም መሪዎቻቸው ሕዝቡን በማስተባበር ትግሉን መምራት ይጠበቅባቸዋል።ሕዝቡም ከጎናቸው በመቆም የትግሉን ቀጣይነት ማረጋገጥ ይኖርበታል። በዚህ በኩል በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ የድርሻውን እንደሚወጣ ቃል ይገባል። ለመምህራንም በትግሉ ላይ እንዲሳታፉ በድጋሚ ጥሪ ያስተላልፋል።*

*ሀሰባቸውን በሰላማዊ መንገድ ለመግለጽ በወጡ ዜጎች ላይ ወያኔ/ኢህአዴግ  ያደረሰውን የአካልና የሞራል ጉዳት ፣ያሳያውን ሕገወጥነትና የጭካኔ እርምጃ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ በጥብቅ ያወግዛል። ሰላም ወዳድ መንግሥታት፣ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶችና አገርወዳድ ኢትዮጵያውያን ይህን እኩይ ተግባር እንዲቃወሙና ከተበዳዩ ሕዝብ ጎን እንዲቆሙ ጥሪ ያቀርባል።*

*የሕዝብ ስቃይ ያብቃ!!*
*ሁሉም ለበቱ ዘብ ይቁም!!*
*ለትግል እንነሳ፤ በወያኔ ላይ እናምጽ!!*